# ልጄን ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ምን ያስፈልገኛል?



## 1
### የልጄ የልደት ምሥክር ወረቀት



የልጁ **ዋና ቅጂ** ወይም **የተረጋገጠ** የልደት ምስክር ወረቀት።

## 2
### የወላጅ ፎቶ ያለው መታወቂያ



የወላጅ ወይም የሕጋዊ አሳዳጊ ፎቶ ያለው መታወቂያ።

## 3
### የአሳዳጊነት መረጃዎች



የአሳዳጊነት መረጃች ፣ **አስፈላጊ ከሆነ።**

## 4
### የትምህርት ቤት ሰነዶች



ከሌላ የትምህርት ስርዓት ወይም ከሌላ ሃገር የትምህርት ቤት ሕጋዊ ሰነዶች **(አስፈላጊ ከሆነ/ካለ)።**

## 5
### የሕክምና ሰነድ



**የክትባት ሰነድ፣ አካላዊ ምርመራ (K-5) እና የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ።** ትምህርት ከመጀመሩ **ከ12 ወራት** በፊት የተደረገ።

## 6
### የነዋሪነት ማረጋገጫ



**ባጠቃላይ ሶስት ሰንዶች ማቅረብ ያስፈልጋል።** ለበለጠ መረጃ ከጀርባ ይመልከቱ።

# ልጄን ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ምን ያስፈልገኛል?



## የነዋሪነት ማረጋገጫ – ባጠቃላይ 3 ማቅረብ ያስፈልጋል

### ከሚከተሉት ውስጥ 1 :-



- **<u>የኪራይ ውል ስምምነት:-</u>** ዋናው የስምምነት ውል ግዜው ያላላፈበት መሆን አለበት እንዲሁም ቀን፣ ግዴታዎች፣ ስሞች፣ ፊርማዎች፣ ተማሪውን የሚያስመዘግብ ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ የቤት አድራሻ የያዘ መሆነ አለበት።
- **<u>የባለቤትነት ማረጋገጫ:-</u>** የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ከባለቤቱ የግል ንብረት ግብር ቅጂ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት። የባለቤትነት ማረጋገጫው በወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊው ስም መሆን አለበት።
- **<u>ሞርጌጅ:-</u>** ከምዝገባው ወይም ከመጀመርያ የሞርጌጅ ኮትራክት በ60 ቀኖች ውስጥ በአበዳሪው የተዘጋጀ የሞርጌጅ ሰነድ (ቀን፣ አሌክሳንድሪያ ውስጥ የሚገኝ አድራሻ፣ የአበዳሪ ስም ያካተተ) እንዲሁም ግዜው ያላላፈበት የባለቤቱ የንብረት ግብር ቅጂ ጋር መቅረብ አለበት።

## 2 ደጋፊ ሰነዶች:-



- **የአገልግሎት ክፍያዎች** (ውሃ፣ ጋዝ፣ ኤለክትሪክ፣ ኬብል እና/ወይም የቤት ስልክ የአገልግሎት ክፍያ)። ባለፉት *30* ቀናት የተከፈለ መሆን አለበት።
- **ግዜው ያላላፈበት የአሌክሳንድሪያ ከተማ የግል ንብረት ግብር** (መኪና፣ አርቪ፣ ጀልባ)። ያስተውሉ:- የቨርጂንያ የሞተር ተሽከርካሪ መምርያ ሁሉም የግል ንብረቶች ወደ አከባቢው በተዛወሩ በ60 ቀናት ውስጥ በአዲሱ አድራሻ እንዲመዘገቡ ያዛል።
- **ከመንግስት መስሪቤት የተላከ ደብዳቤ:-** (TANIF, HUD, ARHA, IRS, etc.) ደብዳቤው ወደ ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ የተላከ መሆነ አለበት።
- **የቅርብ ግዜ የደሞዝ ክፍያ ማረጋገጫ:-** (የአሌክሳንደርያ ከተማ አድራሻ ያለው እና የቨርጂንያ ግብር ተቀናሽ የሚያሳይ)
- **የቅርብ ግዜ የፌደራል/የግዛት(state) የገቢ ግብር ተመላሽ** የአሌክሳንድሪያ ከተማ አድራሻ ያለው
- በአሌክሳንድሪያ ከተማ ወደሚገኝ አድራሻ የተላከ **ሁለት (2) ተከታታይ የባንክ ሂሳብ መግለጫዎጽ (bank statements)**
- የአሌክሳንድሪያ ከተማ አድራሻ ያለው **ግዜው ያላለፈበት የቤት ባለቤት ወይም የአከራይ የኢንሹራንስ ፖሊሲ**

## የጋራ መኖርያ

ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ **ከሌላ ሰው ጋር የሚኖር ከሆነ በሕግ የተረጋገጠ የጋራ መኖርያ ፎርም (<u>Shared Housing Form</u>) መሙላትና** ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ እና ልጁ/ልጆቹ አብረውት የሚኖሩ ሰው **የሞርጌጅ ዋና ቅጂ፣ የባሌበትነት ማረጋገጫ (ታክስ የተከፈለበት ማረጋገጫ ጋር) ወይም የኪራይ ውል ስምምነት ዋና ቅጂ** ማቅረብ አለበት። በተጨማሪም ወላጅ/ሕጋዊ **ሁለት ደጋፊ ሰነዶች** (በወላጅ/በሕጋዊ አሳዳጊ ስም ያለ) ማቅረብ አለበት።

ACPS Alexandria City Public Schools